# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# ዘመን ተሻጋሪው የቃሊቲ አንድ ኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ

ጽጌረዳ ጫንያለው

መንግሥት ኃላፊነት ወስዶ ከሚሠራቸው ሥራዎች መካከል ለኅብረተሰቡ መሠረተ ልማት በመስፋፋትና በማዳረስ ረገድ ያሉ ክንውኖች ዋነኞቹ ናቸው:: ከእነዚህ የልማት ሥራዎች መካከል አንዱ የኤሌክትክ ኃይል በከተማና በገጠር አካባቢዎች ለማዳረስና ለማስፋፋት የሚሠሯቸው የማስፋፊያ ጣቢያዎች ሲሆኑ፤ የኤሌክትሪክ ኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ መስፋፋትና ያለውን ጠቀሜታ እንዲሁም በየጣቢያዎቹ የሚሠሩ ተግባራት ምን ይመስላሉ የሚሉትን በማንሳት በቃሊቲ አንድ የኤሌክትሪክ ኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ ያለውን እንቅስቃሴ በዛሬው እትማችን ልናስቃኛችሁ ወደናል:: ይህንን ጉዳይ በስፋት ያብራሩልን ደግሞ የጣቢያው የኦፕሬሽንና ጥገና ሠራተኛ ኢንጂነር አስማረ አለሙ የነገሩንን እንደሚከተለው አቅርበነዋል:: ቃሊቲ አንድ የኤሌክትሪክ ኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ የተቋቋመበት ምክንያት የቆቃ ኃይል ማመንጫ ጣቢያን ተከትሎ ነው:: የቆቃ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ተገንብቶ ያለቀው በ1952 ዓ.ም ሲሆን፤ በዚሁ ዓመተ ምህረት ቃሊቲ አንድ የኤሌክትሪክ ኃይል ማከፋፈያ ጣቢያም ተግንብቶ አልቆ በአንድ መስመር 132 ኪሎ ቮልት ወደ እዚህ ጣቢያ ይመጣ ነበር:: ይሄ ጣቢያ ደግሞ በሁለት ትራንስፎርመሮች ያንን ኃይል ተቀብሎ በ132 ኪሎ ቮልት በአዲስ አበባ ከተማ ሜክሲኮ ወደሚገኘው የኃይል ማፋፈያ ጣቢያ እንዲገባ ያደርጋል::

**የኃይል ማመንጫ ያለ ማከፋፈያ ጣቢያዎች ምንም ነው:: የሚያመነጨውን ኃይል አድራሽ ቦታ ያስፈልገዋል**

የቆቃ የኃይል ማመንጫ መገንባት አዋሽ አዋሽ ሁለትና ሦስት ተብለው የሚጠሩት የኃይል ማመንጫዎች እንዲገነቡ አስችሏል:: ይህም የአዋሽ ሁለትና ሦስት ማመንጫዎች ቆቃ ኃይል ማመንጫ ኤሌክትሪክ አመንጭቶ በሚወጣው ውሃ ኃይል እንዲያመነጩ ታስበው የተገነቡ መሆናቸውን ያብራራሉ::

የኃይል ማመንጫዎች ግንባታ በቀላል ወጪ የሚከናወን እንዳልሆነ የሚያነሱት ኢንጅነር አስማረ፤ ከዚህ አኳያ በአንድ ጊዜ ብዙ ኃይል ማመንጫ መሥራት አዳጋች ነው:: ስለዚህም አዋሾች ከተሠሩ በኋላ የፊንጫ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ እንዲገነባ ሆኗል:: ፊንጫ በሦስት ጀነሬተሮች ያመነጨው ኃይል ደግሞ ወደ ገፈርሳ በ230 ኪሎ ቮልት ይገባል:: ከገፈርሳ ደግሞ ወደ ቃሊቲ አንድ በሁለት መስመሮች በ132 ኪሎ ቮልት እንዲገቡ ተደርጓል:: ይህ ደግሞ ከፊንጫም የምንቀበለው ኃይል እንዳለ ያሳየናል ይላሉ::

ከፊንጫ በኋላ መልካ ዋከና የተሠራ ሲሆን፤ ከዚህም በሁለት መስመሮች በ132 ኪሎ ቮልት ኃይል እንድናገኝ ሆነናል የሚሉት ኢንጅነሩ፤ ከ1980 ዓ.ም በኋላ ቢሆን የተለያዩ የማስፋፊያ ሥራዎች መሠራታቸውን ያነሳሉ:: ይህም ጊቤ አንድ ተሠርቶ ወደ ሰበታ ኃይል ማመንጫ የገባውና ከዚያ ወደ እነርሱ ጣቢያ የሚገባው 230 ኪሎ ቮልት መሆኑን ያስረዳሉ:: ሌላው ደግሞ ጣና በለስ ሲሆን፤ በለገጣፎ ማከፋፈያ ጣቢያ በኩል 230 ኪሎ ቮልት ኃይል እንዲገባ ሆኗል:: ስለዚህም በዚህ ዓይነት ሁኔታ እያደገ ሄዶ አሁን ያለው አቅም በ230 ትራንስፎርመሮች ተቀብለው ወደ 132 ኪሎ ቮልት በመቀነስ ወደ ጣቢያው የሚያስገቡት 375 ሜጋ ቮልት፤ በባለ 132 ኪሎ ቮልት መስመር 22 ሜጋ ቮልት፤ በ15 በኩሉ ደግሞ 63 ሜጋ ቮልት፤ በ33ቱ ደግሞ 50 ሜጋ ቮልት አለ:: እናም የእነዚህ ድምር ውጤት መሆኑን ይናገራሉ::

የኃይል ማመንጫ ያለ ማከፋፈያ ጣቢያዎች ምንም ነው:: የሚያመነጨውን ኃይል አድራሽ ቦታ ያስፈልገዋል:: ኃይል ጣቢያው ላይ ከደረሰ በኋላ እንደየ አስፈላጊነቱና እንደየአካባቢው ነዋሪ ፍላጎት የማከፋፈል ሥራ ይሠራል:: ስለዚህ የጣቢያው መስፋፋት ወይም ደግሞ ከፍተኛ ኃይል እንዲቀበል ማድረግ ለአካባቢው ተጠቃሚ ፍላትን ለማሟላት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው:: ለዚህ ደግሞ የጣቢያዎች መስፋፋት እጅጉን ጠቅሞናል ይላሉ::

‹‹ያለንን ነው የምንሰጠው የሌለንን ልንሰጥ አንችልም::›› የሚሉት ኢንጅነሩ፤ የጣቢያው አቅምን ያሳደጉት የኃይል ማመንጫዎች መስፋፋት ነው:: ምክንያቱም ኃይል ማመንጫዎች በብዙ ቁጥር ከየኃይል ማመንጫዎቹ ወደ እነዚህ ማከፋፈያ መስመር ይገባሉ:: በዚህ ደግሞ የማከፋፈያ ጣቢያውን አቅም ያሳድገዋል:: የጣቢያዎች መስፋቱ እንደዚህ ዓይነት ወጪዎችን (ኃይልን ለማሠራጨት) ለማብዛት ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደአለውም ያብራራሉ::

ኢንጅነር አስማረ፤ ብሔራዊ ቋት የሁሉንም ማከፋፈያ ጣቢያዎችንና የኃይል ማመንጫዎችን የሚቆጣጠር በመሆኑ የትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ላይ በአቅራቢያው ያለው የኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ ችግር ቢገጥመው ነዋሪዎች በጭለማ ውስጥ እንዲቀመጡ አይሆኑም:: ምክንያቱም ከዋናዎቹ ማከፋፈያ ጣቢያዎች ኃይል የሚያገኙበት ዕድል ይፈጠራል:: ስለዚህም የኃይል ጣቢያዎች መያያዛቸው የኃይል አቅርቦቱን በማፋጠን ለችግሮች እልባት ለመስጠት ያስችላልም ሲሉ ያስረዳሉ::

ጣቢያው ሥራ ከጀመረ ጀምሮ የተለያዩ ማሻሻያዎችን እንዳደረገ የሚናገሩት ኢንጅነሩ፤ የመጀመሪያው ተግባሩ በጀርመኖቹ የተተከሉት መቆጣጠሪያ መሣሪያዎች በማርጀታቸው የተነሳ ጣቢያው ዘመኑን በሚመጥን ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች መቀየሩ ነው:: ሌላኛው ደግሞ በራሽያ እርዳታ የተሠራው መልካ ዋከና ኃይል ማመንጫ ላይ የተከናወነው ተግባር እንደሆነ ያነሳሉ::

ብሬከሮቹ በአየር የሚሠሩ በመሆናቸው አየር ብሬከሮቹን ለማሠራት ከፍተኛ ኃይል ያላቸው አማቂ አየር ያስፈልጋል:: ምክንያቱም ብረትና ብረት ስለሆነ የሚገናኘው ፍሰት ይኖራል:: ፍሰቱ ደግሞ ያንን የተሞላውን አየር ይጨርሰዋል:: እንደገና አየር ማመቅ (መሙላት) ግድ ይሆናል:: እናም አጠቃላይ ሥራው አሰልቺ ነበርና እርሱን የማቅለል ተግባር ተከናውኗል:: አሁን በሥራቸው ዋና ተግባር የሆነውም ሲሊንደር ወስዶ መሙላት ብቻ እንደሆነም ይገልጻሉ::

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል